# የነፃነት ጥሪ ለስደተኞች በሙሉ

ለተወሰኑ ስደተኞች በዚህ አመት በስጋት እና በካምፕ ውስጥ የመኖር ግዴታ ማብቂያ ይሆናል.(የመኖሪያ ፍቃድ ስለሚሰጥ)
አጠቃላይ የክልሎች የውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሮች በኖቬምበር 16 እና 17 በኑርንበርግ ከተማ ይህንን በሚመለከት ስብሰባ ያደርጋሉ በዚሁ ላይ ይወስናሉ.
በወቅቱ እየተከራከሩ ያሉት ለማን ይሰጥ ለማን ይከልከል በሚለው ሲሆን -መመዘኛም አለው ፣ 1)በሀገር ውስጥ ቢያንስ ስድስት አመት እና ከዚያ በላይ ለሆናቸው 2)የቓንቓ ችሎታ እና ስራ ያላቸው ተበሎ ይገመታል.

ስለዚህ ሁሉም የተሻለና የተስተካከለ የመኖሪያ ፍቃድ እንዲያገኝ በህብረት ሰላማዊ ሰልፍ ከቤተክርስቲያናት፣ከመስጊዶች፣ከተለያዩ ሰብሃዊ ድርጅቶች እና ለስደተኟ መብት ተከራካሪ ቡድኖች ጋር መሰለፍ ይኖርብናል.

ማነው የመኖሪያ ፍቃድ የሚያገኘው ?
የመኖሪያ ፍቃድ መብት መስጫ ደንብ ይወጣል ግን ግልፅ አይደለም
እዚህ ውሳኔ ላይ ለመድረስ በቀዩ ፓርቲ(በሶሻል ዲሞክራቶች )እና በጥቁሩ ፓርቲ(በክርስቲያን ዲሞክራቶች) መካከል ከባድ ውይይት ተደርጓል.

በቅርቡ ያለው መወያያ አርዕስት እንደሚከተለው ይሆናል..
ሀ]የተገባበት ቀን ይህ ማለት ግለሰቡ ምን ያህል ቆይቶል
ለቤተሰብ 6 አመት ለሌጣ ደግሞ 8 አመት በተከታታይ ሀገር ውስጥ ለኖሩ ይላል.

ለ|**ለአቅ-ማዳም** ላልደረሱ
ለእነሱም 8 አመት ሀገር ውስጥ ያለማቋረጥ የኖሩ መሆን ይገባቸዋል

ሐ|**ስራ**
ኑሮውን በስራ የሚደግፍ መብቱ ይሰጠዋል
ይህም እንደሙከራ ጊዜ ይታያል ከ6_9ወራት ባሉት ጊዚያት ስራ ካልያዘ መብቱ ሊቀማ የችላል.

መ|**የቋንቋ** ችሎታ

ቋንቋ የመናገር ችሎታ አስፈላጊ ይሆናል መፃፍ ግን ግዴታ አይሆንም
ቋንቋ ለመናገር መሞከሩ አይከፋም
ሠ|ወንጀል
በወንጀለኝነት የተሰማራ የመኖሪያ ፍቃድ አያገኝም ከ60እስከ90 ቀናት ተፈረደበት.
ረ| በየጊዜው ያልተስተካከለ(የተምታታ) መረጃ ላቀረበ ወይም የተሳሳተ መታወቂያ ላቀረበ

## ሐገሮችን በተመለከተ

1|**ኢራቅ**
ከኢራክ የመጡ ስደተኞች በአዲሱ ህግ የመኖሪያ ፍቃድ አያገኙም።

እንዲሁም ወደ ሰሜን ኢራቅ (ኪርኩክ)ለመመለስ እየታሰበነው ይባላል።
2|**አፍጋኒስታን**
ከሀንቡርግ እንደመለሱ ሁሉ ከተለያዩ ክልሎች መመለስ ይጀምራሉ ይባላል።

3|**ከምዕራብ አፍሪካ** (ከናይጄሪያ፣ከቶጎ፣ከቤኒን፣ከጊኒ፣ከቡኪናፋሶ)
ለመጡ ስደተኞች የመኖሪያ ፍቃድ የማግኘት ዕድሉ በጣም የመነመነ ነው።

4|**ኢትዮጵያ እና ኤርትርያ**
ከኢትዮጵያ ከኤርትርያ ለመጡ ስደተኞች አንዳንድ ወሬዎች እንደሚሰሙት፣ የሁለቱ ሀገሮች ኤምባሲዎች በቅርብ ጊዜ ለተቃዋሚ ድርጅት አባላት ከሐገር ሊያስወጣ የሚያስችል ሊሴ ፓሴ እንዳዘጋጁ ይነገራል።

**የመኖሪያ ፍቃድ ለተነፈጉ ዕጣው ምን ይሆን?**
ለተወሰኑ ስደተኞች ማለትም ለ50.000 ለሚሆኑ(በባየር የውስጥ ጉዳይ
ሚኒስትር ሚ|ር ጉንተር ቤክሽታን አባባል)የመኖሪያ ፍቃድ ይሰጣል።
ለተቀሩት ሁኔታቸው እንዳለ ይቀጥላል እንዲሁም የከፋ ይሆናል።

ይህም እስከዛሬ ይቻል የነበረው ለምሳሌ ዝም ማለት ወይም ወደ ኤምባሲ
ላለመሔድ ተቃውሞ ሕጉ ከወጣ  በxላ እስር ቅጣት ሊያስከትል ይችላል

**ታድያ ምን መፍትሔ አለ?**
ይህ ዛሬ የመኖሪያ ፍቃድ ለመወሰንና ለመቋጨት የተደረሰው
እንዲያው በፍላጎትና በሐዘኔታ በመነሳሳት አይደለም/
በብዛት በሚቆጠሩ የየአካባቢ በጎ አድራጊ ድርጅቶችና ግለሰቦች ጥረትና
ግረት ነው=ከዚህም በተጨማሪ ግለሰቡ እራሱ ለትግሉ ያበረከተው አስተዋፅኦ፣ለምሳሌ ሜክለንቡርግ
ፎርፖመን(Mecklenburg-Vorpommern)
አንድ የቶጎ ዜጋ ወደ ሀገሩ ሊላክ ሲል በአካባቢው በአሉት የሰብአዊ መብትና የበጎ-አድራጎት ድርጅቶች
ትብብር አማካይት የመላኩ ሁኔታ ከሽፏል።
ስለዚህ በየአካባቢ ባሉት ቡድኖች አብሮ የተቃውሞ ድምፅ ማሰማቱ ሁሉም
የመኖሪያ ፍቃድ እንዲያገኝ ያስችላል።

**ሠላማዊ ሰልፍ**

ሠላማዊ ሰልፍ በተመለከተ እንደሀገሩ ይለያያል
ጀርመን ሀገር በሚመለከት የሚከተለውን የመልከቱ፤

**እንደስደተኝነቴ ሠላማዊ ሰልፍ መውጣት እችላለሁን?**
ማንኛሁም ግለሰብ ሠላማዊ ሰልፍ የመውጣት መብት አለው ሕጋዊም ነው
ይህም ሕግ መንግስት ላይ የፀደቀ ነው።

**ሠላማዊ ሰልፍ መሳተፍ ጉዳዬን ያስተጓጉላል?**
የስደተኛ ጉዳዩ እና ሠላማዊ ሰልፉ የሚያገናኛቸው ነገር የለም.

**ሠላማዊ ሰልፍ ላይ የፖሊስ መገኘት ምን ያምጣል**
በጀርመን ሀገር ውስጥ የሚደረግ ማንኛውም ሕጋዊ ሠላማዊ ሰልፍ
በደንብ ልብስና ዩኒፎርም በለበሱ  ፖሊሶች ይታጀባል.በአጠቃላይ
በቅርብ ጊዜ እንደታየው በፖሊሶችና ሠላማዊ ሰልፍ በወጡ ስደተኞች
መካከል ፈፅሞ ግብግብ ተፈጥሮ አያውቅም።

ሰለዚህ በሕብረት መኖሪያ ፍቃድ መጠየቂያ ሰላማዊ        ተዘጋጅቶል
15-18 ኖቬምበር -JOG-Kongress ኑረንበርግ ውስጥ
ሙሉ ኢንፎርሜሽን www.bleiberechtsbuero.de
16 ኖቬምበር ጀርመን አቀፍ ሠላማዊ ሰልፍ 16.30
ቦታው Lorenzkirche በሙዚቃ እና በትያትር የሚያጅቡ
GRIPS(Berlin),Microphone mafia(Hip-Hop Köln)
16 እና 17 ኖቬምበር እዚሁ የየክልሉ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ተጠሪዎች
ተሰብስበው ሕጉን ያፀድቃሉ።